የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፷፱
አዲስ አበባ ግንቦት ፲፮ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

17[th] Year No. 69
ADDIS ABABA 24[th] May 2011

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፪፻፵፩/፪ሺ፫
የጎንደር ዩኒቨርሲቲ እንደገና ማቋቋሚያ
የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ...........ገጽ ፭ሺ፰፻፹፯

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፵፩/፪ሺ፫

### <u>የጎንደር ዩኒቨርሲቲን እንደገና ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፩ አንቀጽ ፭ እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶/፪ሺ፩ አንቀጽ ፭(፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል::

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ ደንብ "የጎንደር ዩኒቨርሲቲ እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፵፩/፪ሺ፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

**፪. <u>መቋቋም</u>**

፩/ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ እንደገና ተቋቁሟል::

፪/ የዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል ::

፫/ ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶/፪ሺ፩ እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፲/፪ሺ፫ መሠረት ይተዳደራል::

## CONTENTS

Regulation No. 241/2011
Gonder University Re-establishment
Council of Ministers Regulation ...............Page 5887

## <u>COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 241 /2011</u>

### <u>COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE RE–ESTABLISHMENT OF THE GONDER UNIVERSITY</u>

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 and Article 5 (1) of the Higher Education Proclamation No. 650/2009.

**1. <u>Short Title</u>**

This Regulation may be cited as the "Gonder University Re-establishment Council of Ministers Regulation No. 241 /2011"

**2. <u>Establishment</u>**

1/ The Gonder University (hereinafter the "University") is hereby re-established as an autonomous higher education public institution having its own legal personality.

2/ The University shall be accountable to the Ministry of Education.

3/ The University shall be governed by the Higher Education Proclamation No. 650/2009 and the Federal Universities Council of Ministers Regulation No. 210/2011.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O. Box 80,001

፫. <u>ዋና ግቢ</u>

የዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ በጎንደር ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

፬. <u>የተሻረ ደንብ</u>

የጎንደር ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፲፪/፲፱፻፺፮ በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

፭. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ግንቦት ፲፮ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

3. **<u>Main Campus</u>**

The University shall have its main campus at Gonder and may establish elsewhere other academic units and centers of research and community services .

4. **<u>Repealed Regulation</u>**

The Gonder University Establishment Council of Ministers Regulation No. 112/2004 is hereby repealed.

5. **<u>Effective Date</u>**

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 24th day of May , 2011.

MELES ZENAWI
PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት